DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በጸደይ 2022፣ የእርስዎ ልጅ በስቴት-ደረጃ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት/ የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ (እንግልሽ ላንጓጅ አርትስ) (ELA) እና/ወይም ሂሳብ ወስዷል/ወስዳለች። የእኛ አመታዊ ምዘናዎች ለተማሪዎቻችን በጣም አስፈላጊ የሆኑ እውቀት እና ክህሎቶችን ይለካሉ – ክህሎቶች እንደ መጻፍ፣ ችግር መፍታት፣ እና ሌሎች በሂሳብ እና ELA መተማመን እና ስኬትን የሚያመጡ መሰረታዊ ክህሎቶች።

ልጅዎ ላጠናቀቀው እያንዳንዱ ምዘና ከልጅዎ ትምህርት ቤት የውጤት ሪፖርት ያገኛሉ። ይህ መምሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊማሩ የሚችሏቸውን አስፈላጊ ነጥቦችን ይመራዎታል እና ልጅዎ በቀጣይ አመት ለማሻሻል እንዲረዳው ግብአቶችን ያቀርብልዎታል። የልጅዎ የውጤት ሪፖርቶች ካልደረሱዎት፣ እባክዎ ቅጂውን ለመጠየቅ፣ ልጅዎ በ2021-22 የተማረበትን/ችበትን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

የልጅዎ ውጤት፣ እንዲሁም የዲስትሪክቱ እና የስቴቱ አማካዮች፣ በዚህ አመት እርስዎ ከጠበቁት ያነሰ ሊመስል እንደሚችል እባክዎ ያስተውሉ። ይህ ከኮሮናቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ፣ የትምህርት ስርዓት እና የተማሪዎች መማር ላይ ጉልህ ተግዳሮቶችን ያመጣው፣ መጀመር በኋላ የስቴት-ደረጃ ምዘናዎች የተሰጡበት የመጀመሪያ ዓመት ነው። የዚህ ዓመት ውጤቶች የአካዳሚክ ማገገሚያን እንዴት በጥሩ ሁኔታ መደገፍ እና መገንባት የሚጀመርበት አዲስ የአፈጻጸም መሰረት ማቋቋም እንደሚቻል በተመለከተ የትምህርት ቤቶች ውሳኔዎችን ያሳውቃሉ።

የምዘና ነጥቦች የልጅዎን ሙሉ የአካዳሚክ ታሪክ እንደማይናገር እኛ እናውቃለን። ውጤቶቹ ከብዙ መለኪያዎች ውስጥ አንዱ ነው-የሪፖርት ካርድ ውጤት፣ የክፍል-ውስጥ አፈጻጸም፣ እና የአስተማሪ ግብረመልስን የሚያካትት- ሁሉም ባንድ ላይ ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን እድገት ምስል የሚፈጥሩ ናቸው። በዚያ ምስል ውስጥ፣ አመታዊ ምዘናዎቹ እርስዎ እና የልጅዎ አስተማሪዎች የእርስዎ ልጅ ባለፈው አመት ለELA እና ሂሳብ የመንግስት የይዘት መስፈርቶች ልጅዎ ያሳየውን እድገት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ የተሰሩ ናቸው። እንዲሁም ትምህርት ቤቶች የሁሉም ተማሪዎች ፍላጎቶችን ለመደገፍ ምን ዓይነት ቁሳቁሶች እንደሚፈልጉ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ግምገማዎች ይረዳሉ።

የልጅዎ የELA እና የሂሳብ ምዘናዎች ውጤት ልጅዎ በደምብ እየሰራ ያለውን እና ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልገውን ለማሳየት ተከፋፍሏል። በቀጣይ አመት፣ የልጅዎ አስተማሪዎች ይህን መረጃ ተጨማሪ እርዳታ ለመስጠት ወይም አስፈላጊ ሲሆን የበለጠ ፈታኝ ስራን ለመስጠት ይጠቀሙበታል። በተጨማሪ እርስዎ ይህን መረጃ በቤት ውስጥ የመማር ጊዜን ለማተኮር ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

በመጨረሻ፣ የኛ እቅድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን እና ህልሞቻቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን ለማሳካት መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ነው። አጠቃላይ ጥያቄዎች ካልዎት ወይም ስለምዘናዎች የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የኛን ድህረገጽ ይጎብኙ በ osse.dc.gov/parcc ወይም ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይወያዩ። በተጨማሪ በዚህ መምሪያ ገጽ 4 ላይ ያሉትን ግብአቶች መጠቀም ይችላሉ።

OSSE ውስጥ፣ ሁሉም ተማሪዎች ሊማሩ እና ከፍተኛ ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ እናውቃለን እና ልጅዎ እንዲሳካለት ከእርስዎ ጋር የአጋርነት እድሉን እናደንቃለን።

እናመሰግናለን፣

ዶ/ር ክርስቲና ካንግ
የDC የመንግስት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ

# የውጤት ሪፖርቱን መከፋፈል፥ የፊት ለፊት

ይህ መምሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊማሯቸው የሚችሉትን አስፈላጊ ነጥቦች ይመራዎታል። በተጨማሪም ልጅዎ በመጭው አመት የእርሱን ወይም የእርሷን አፈጻጸም እንዲያሻሽሉ የሚረዳ ጠቃሚ ግብአቶችን ይሰጥዎታል።



## Mathematics

**Scott Testtaker** | **Grade 7 Math Assessment Results**

Anywhere Middle School | District of Columbia Public Schools

**About This Assessment**

1

...t took the Partnership for Assessment of Readiness for College and Careers ...CC) assessment in Mathematics (Math) in Spring 2022. PARCC asks ...nts to think critically, solve problems, and respond to questions that ...ure the knowledge and skills needed for success in this grade or course, ...ltimately in college and careers. These results are one of several ways to ...erstand Scott's needs and strengths. Based on this information, families may work with teachers and schools to identify resources to provide their child support. Schools may use the information in this report to better plan instruction and enrichment for students in the coming year.

If you have questions about this report, please talk to Scott's teacher or principal or contact District of Columbia Public Schools at (202) 724-4593. If you have questions about the PARCC test, please contact OSSE at (202) 719-6500.

**How Can You Use This Report?**

This report will help you answer questions about the development of Scott's skills:

- How did Scott score?
- What are Scott's strengths and areas for improvement in this subject?
- How did Scott's score compare to that of other students?

**How Did Scott Perform on This Math Assessment?**

2

...s section shows your student's overall score on the assessment. This overall score determines which performance level ...student is in.

**Performance Level**

Level 4

**Score**

760

**Students who score in Level 4**

met expectations

**for Grade 7 Math learning standards.**



Level 1 Did Not Yet Meet Expectations
Level 2 Partially Met Expectations
Level 3 Approached Expectations
Level 4 Met Expectations*
Level 5 Exceeded Expectations*

*Levels 4 & 5 indicate being on track for the next grade level course and on track to leave high school college and career ready

**Want to know more?**

Turn to the next page to learn about how Scott performed on key areas of the assessment and how Scott's results compare to those of other students.

## 1) የምዘና መግለጫ

የምዘናው አጭር መግለጫ በሪፖርቱ በላይኛው ክፍል ይገኛል። ስለዚህ ሪፖርት ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ በአንቀጹ ታችኛው ጥግ ላይ ማግኘት ያለብዎት ሰው መረጃ አለ።

## 2) ልጅዎ በአጠቃላይ አፈጻጸሙ እንዴት ነው?

የልጅዎ ውጤት ከአምስቱ የአፈጻጸም ደረጃዎች አንዱ ላይ ያርፋል። የአፈጻጸም ደረጃዎቹ ልጅዎ ለክፍሉ ደረጃ የሚጠበቅበትን/የሚጠበቅባትን ማሟላቱን/ማሟላቷን ይለያል። ደረጃ 4 ወይም 5 ውጤት ማለት ልጅዎ በዚያ የትምህርት አይነት የሚጠበቅበትን አሟልቷል ወይም ከሚጠበቅበት በላይ ሰርቷል ማለት ነው። በተጨማሪም ለቀጣይ የክፍል ደረጃ መስመር ላይ ናቸው ማለት ነው። ከደረጃ 4 በታች ውጤት ያላቸው ተማሪዎች አሁንም የክፍሉን ደረጃ ክህሎቶችን እና እውቀት እያዳበሩ ሊሆን ይችላል።

# የውጤት ሪፖርቱን መከፋፈል፥ የጀርባ

## 3) ልጅዎ ልዩ እውቀት እና ክህሎቶችን ምን ያክል ጥሩ አድርጎ/ጋ ተማረ/ቹ?

ተማሪዎች በተለያዩ ክፍሎች ስለ ጥንካሬዎቻቸው እና ሊያስፈልጋቸው ስለሚችል ተጨማሪ እርዳታ የበለጠ ዝርዝር መረጃ ያገኛሉ። ይሄ ክፍል ልጅዎ ለእያንዳንዱ የምዘናው ቁልፍ አካል የሚጠበቅባቸውን ያሟሉ ወይም ያለፉ፣ የሚጠበቅባቸው ነገር ላይ የደረሱ፣ ወይም በከፊል የሚጠበቅባቸውን ያሟሉ ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር ምን ዓይነት አፈጻጸም እንዳመጣ/ች ያሳያል።



**Grade 7 Math Details**

**Performance Level**
Level 4

**How Did Scott Perform On Key Areas of the Assessment?**

3

...ents who performed at Level 4 overall on this assessment met learning expectations and are likely prepared for the next grade or course. This ... shows if your child performed about the same as students who met or exceeded expectations, approached expectations, or did not yet meet or ...y met expectations for each key part of the assessment.

| Major Content | Additional & Supporting Content | Expressing Mathematical Reasoning | Modeling & Application |
|---|---|---|---|
| Proportions, operations with rational numbers, algebra | Circumference, area, volume, statistics, probability | Justify solutions and analyze/correct others' reasoning | Represent and solve problems using symbols and tools |
| Meets or Exceeds ✓ | Meets or Exceeds ✓ | Nearly Meets ● | Nearly Meets ● |

✓ Meets or Exceeds Expectations ● Nearly Meets Expectations ▬ Below Expectations

**How Did Scott's Performance Compare?**

4

Scott scored better than 71% of students in Anywhere Middle ...l who took the Grade 7 Math test.

Scott scored better than 66% of students in District of Columbia Public Schools who took the Grade 7 Math test.

Scott scored better than 75% of students in DC who took the Grade 7 Math test.



**What Is Next?**

Bring this report to your next conference with your student's teacher. You can ask Scott's teachers:

- What is Scott learning in math this year?
- How is Scott doing?
- How can I use this information to work with Scott this year?
- What resources should I use to support Scott?

**Where Can You Find More Information?**

5

- How Scott's school and other schools scored:
  Visit www.OSSE.dc.gov/parcc, or call OSSE at (202) 719-6500
- How the test is designed and what it measures:
  Visit www.OSSE.dc.gov/parcc, or call OSSE at (202) 719-6500
- How families, educators, and schools use these reports:
  Visit www.OSSE.dc.gov/parcc, or call OSSE at (202) 719-6500

OSSE

## 4) ልጅዎ ከሌሎቹ ተማሪዎቹ ጋር ሲነጻጸር ምን ዓይነት አፈጻጸም ነበረው/ነበራት?

ይህ ሪፖርት በትምህርት ቤት ደረጃ፣ የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲ ደረጃ፣ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ የልጅዎ አፈጻጸም ከእኩዮቻቸው ጋር እንዴት እንደሚነጻጸር ያሳያል።

## 5) ቀጥሎ ምንድን ነው?

በውጤት ሪፖርቱ ላይ ያለው መረጃ የተማሪውን አፈጻጸም ለመለካት እና የክህሎት ማዳበሪያ መምሪያን ለመስጠት ለሁለቱም የታለመ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን አስተማሪ ስለ ልጅዎ አፈጻጸም ሊጠይቋቸው የሚችሉ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ያቀርባል። በተጨማሪ የበለጠ መረጃ የት ማግኘት እንደሚችሉ ያጋራል።

# ግብአቶች እና ድጋፍ

ከታች ያሉት ልጅዎ በELA እና ሂሳብ እንዲያድግ/እንድታድግ የሚረዱ ጠቃሚ ግብአቶችን፣ እንዲሁም ውጤቱን ከልጅዎ እና ከልጅዎ አስተማሪ ጋር የሚወያዩበትን ጠቃሚ ምክሮች ናቸው።

## ስለየDC PARCC ውጤቶቹ ወይም ስለ PARCC ምዘና የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?

ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን ድህረገጾች ይጎብኙ፣ ስለ PARCC ምዘናዎች እና የኮመን ኮር የስቴት ደረድዎች፥

- OSSE.dc.gov/parcc ስለ DC-የተለየ መረጃ በውጤት ሪፖርቶች፣ PARCC ምዝናዎች እና የኮመን ኮር የስቴት ደረጃዎች።
- OSSE.dc.gov/parcc የተማሪዎ ትምህርት ቤት እና በ ዲሲውስጥያሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዴት እንደሰሩ መረጃ ለማግኘት።
- OSSE.dc.gov/parcc ለ ተማሪዎችእና ወላጆች ምዘናዎች እና ግብዓቶች ላይ መረጃ ለ ማግኘት።
- DC.mypearsonsupport.com/practice-tests/ ከክፍል 3 እስከ 11 ላሉ ተማሪዎች የመለማመጃ ፈተናዎች እና ሞዴል ጥያቄዎችን ያቀርባል።
- CoreStandards.org ስለ ኮመን ኮር የ ስቴት ደረጃዎችበተመለከተ የ በለጠ ለመማር።

## አሁን የልጅዎ የፌተና ውጤቶቹን ካገኙ፣ ቀጥሎ ምንድን ነው?

እነዚህን ምዘናዎች በመጠቀም ልጅዎ በአካዳሚክ እንዲያሻሽል እንዲረዳው የሚያስችሉ የተለያዩ ግብአቶች አሉ። እነዚህ ግብዓቶች ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ለመደገፍ ብቸኛ ዓላማ ጠቃሚ መሳሪያዎች እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው። OSSE ዲስትሪክቱ የማሳወቂያ ምክረ-ሀሳቦች በሚታሰቡበት ደረጃ ማንኛውንም እንዲህ ዓይነት ግብዓቶችን አይደግፉም እና/ ወይም ስፖንሰር አያደርጉም።

- GreatSchools.org በቤት ውስጥ ከልጅዎ ጋር ትምህርቶችን እና መልመጃዎችን መስራት እንዲችሉ የይዘት እና ክፍሉን የሚመጥን ቪዲዮዎች ያሳያል።
- BeALearningHero.org ለወላጆችክህሎቶችን ጨምሮ የግብዓቶች ሀብት አለው።
- የገንቢ ገጽ እና የመማሪያ መሳሪያዎች ገጽ፣ ዲሲ'ን መሰረት ላደረገ ክፍል፣ የትምህርት ዓይነት እና የይዘት ዙሪያ ግብዓቶችን ይበጃል።

## ልጅዎን ስለእርሱ ወይም እርሷ ነጥብ ሊያዋሩ ይፈልጋሉ?

ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ለማውራት ኤክስፐርቶቹ ናቸው። የልጅዎ የፈተና ውጤትን አስመልክቶ ሲነጋገሩ ከታች ያሉትን የተወሰኑ ጠቃሚ ነገሮች ማስታወስ ተገቢ ነው፣

- የፈተና ውጤቶች የአፈጻጸም አንዱ መለኪያ ብቻ ነው።
- ማተኮር ጥንካሬዎች ላይ።
- ሊያድጉ ስለሚገባቸው ክፍሎች ስትራቴጂዎችን መወያየት (ለምሳሌ፣ ኦንላይን ልምምድ፣ ከአስተማሪ ጋር መስራት)።

## የልጅዎን ነጥብ በተመለከተ የልጅዎን መምህር ሊያዋሩ ይፈልጋሉ?

ከታች ከልጅዎ አስተማሪ ጋር የሚያደርጉትን ንግግር ለመምራት የሚረዳ የተወሰኑ ጥያቄዎች ናቸው፣

- በዚህ አመት የልጄ የሂሳብ የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? በ ንባብ?
- ልጄ በሂሳብ ክፍል አፈጻጸሙ/ሟ እንዴት ነው? በእንግሊዘኛ ቋንቋ አርትስ?
- ልጄ እነዚህን ግቦች ለማሟላት በትምህርት ቤት እና በቤት ምን ዓይነት ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልገዋል ወይም ያስፈል ጋታል?
- በእርስዎ ምልከታዎች፣ ልጄ በደምብ የሚሰራው ምንድን ነው? ልጄ ሊያሳድገው/ልታሳድገው የሚገባ/ት የተወሰኑ ዘርፎች ምንድን ናቸው?